## ማን ነው MMR/የኩፍኝ/ጀሮደግፍ/ጀርመን ኩፍኝ ክትባት መውሰድ የማይገባው?

ክትባት ከመስጠቱ በፊት በርስዎ የበሽታ መከላከያ አቅራቢ በኩል የቅድመ በሽታ መከላከያ ዝርዝር ሁኔታ ለማጣሪያ ይሞላል። ይህም በሰዎች ያለን አንዳንድ ሁኔታ ለማወቅ ሲሆን ማለት እንደ :

- ቀደም ሲል የMMR ክትባት ወይም የተቀላቀለ በአንድ ክትባት ሲወሰዱ ያለመስማማት የሰውነት መቆጣት አሳይቶ ከሆነ።
- ነብሰጡር ለሆኑ ሴቶች ወይም የበሽታ መከላከያ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ የማርገዝ እቅድ ያላቸው ሴቶች።
- አንድ ሰው ህመም ካለበት ወይም ህክምና ማለት እንደ ኮርቲሶን/cortisone ወይም ፕረድኒሶሎን/prednisolone የሚወስድ ከሆነ የበሽታ መከላከል አቅም አሠራርን ሊያዳክም ስለሚችል።
- አንድ ሰው የበሽታ መከላከያ ክትባቱን በወሰደበት ቀን ትኩሳት ማለት የሙቀት መጠኑ ከ38.5° C በላይ በመሆን ሲሰቃይ ነው።

## በበለጠ መረጃ ለማግኘት

- ከሃኪምዎ ወይም ከርስዎ የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ጋር መወያየት።
- በአካባቢዎ ያለን የመንግሥት በሽታ መከላከያ መስጫ አገልግሎትን መጠየቅ።
- ለእናቶችና የህጻን ጤና ነርስ መጠየቅ።
- የወሊድ መቆጣጠሪያ ክሊኒኮች መረጃ አላቸው።
- በተሻለ የጤና ማስተላለፊያ :
  www.betterhealth.vic.gov.au
- ለኩፍኝ ትምህርት ነርስ፣ መስማት ለተሳነው ፋውንዴሽን/Deafness Foundation
  በስልክ (03) 9887 8683
  በኢሜል rubella@deafness.org.au
  በድረ ገፅ www.deafness.org.au

## በቋንቋ የተተረጎሙ

ይህ ጥራዝ ወረቀት በሌላ የማህበረሰብ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በደፍነስ ፋውንዴሽን/Deafness Foundation ጽህፈት ቤት ይገኛል። በራስዎ ቋንቋ እርዳታ በትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (TIS) በኩል ማግኘት ይቻል ይሆናል። በቁጥር 13 14 50 ላይ በነጻ መደወል።

ሕትመት


Deafness Foundation
(Victoria)
በደፍነስ ፋውንዴሽን
(ቪክቶሪያ)

Deafness Foundation (Victoria)
በደፍነስ ፋውንዴሽን (ቪክቶሪያ)
ፖ.ሳ.ቁጥር/PO Box 42, Nunawading 3131
ስልክ 03 9887 8683  Fax 03 9887 8848
ኢሜል rubella@deafness.org.au
www.deafness.org.au



This leaflet is supported by an unrestricted grant from GlaxoSmithKline (GSK). GSK has had no input into the content of this leaflet.

April 2009


# RUBELLA

AMHARIC





## ለሞላው ማህበረሰብ ስለ ኩፍኝ ጠቃሚ እውነታዎች






## ኩፍኝ/RUBELLA ምድን ነው?

ኩፍኝ/Rubella (እንዲሁም የጀርመን ኩፍኝ/German Measles ተብሎ ይጠራል) በቫይረስ የሚመጣ/የሚተላለፍ ሃይለኛ በሽታ ሲሆን በህጻናት፣ በታዳጊና በጎልማሶች ላይ በሽታው ሊከሰት ይችላል። ይህ ከ measles ኩፍኝ የተለየ በሽታ ሲሆን ለየት ባለ ቫይረስ ይከሰታል። የኩፍኝ በሽታ ምልክት በመጠኑ ትኩሳትን፣ የእጢ እብጠትን፣ የመጋጠሚያ ህመምንና በአንገትና በፊት ላይ የቆዳ ሽፍታ መጀመርን ያካተተ ሲሆን ይህም ለሁለት ወይም ለአራት ቀናት ይቆያል። አንዳንድ ጊዜ የኩፍኝ/Rubella በሽታ ሲከሰት መጠነኛ ምልክቶች ሊኖረው ወይም ላይኖረው ይችላል።

በሴቶች የመጀመሪያ 20 ሳምንታት እርግዝና ላይ የኩፍኝ/Rubella በሽታ በጣም አደገኛ ነው። የዚህ ውጤትም እናት ልታስወርድ ትችላለች ወይም የሚወለደው ህጻን ከችግር ጋር ማለት መደንቆር፣ መታወር፣ የልብ ጉድለትና የአእምሮ ጉዳተኛ ሆኖ ሊወለድ ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲከሰት ኩፍኝ ከተፈጥሮ የመጣ (CRS) ተብሎ ይጠራል።



## እንዴት ኩፍኝ/ RUBELLA ሊስፋፋ/ሊተላለፍ ይችላል?

እንደ ጉንፋን ኩፍኝም/Rubella በተመሳሳይ መንገድ ሊተላለፍ ሲችል ይህም የታመመ ሰው በሚስልበትና በሚያስነጥስበት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል። ብዙ ጊዜ የኩፍኝ በሽታ ምልክት ለመታየት ወደ ሁለት ሳምንታት የሚሆን ይወስዳል እንዲሁም ሰዎች በሽታው እንደያዛቸው ላያውቁ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ እነዚህ ሰዎች በሽታውን ጤነኛ ለሆኑት ማስተላለፍ ሲችሉ፣ ይህም የበሽታ መከላከያ ክትባቱን ላልወሰዱትና በመጀመሪያው የእርግዝና ወቅት ለሆኑት ሴቶች ነው። ያልተወለደ ህጻን በችግር መጋለጥ በመጀመሪያው እርግዝና ጊዜ ነው።

## እንዴት ኩፍኝ/RUBELLA እና በተፈጥሮ የመጣን ኩፍኝ/CRS መከላከል እንችላለን?

ኩፍኝ/Rubella እና በተፈጥሮ የመጣን ኩፍኝ/CRS ለመከላከል ይቻላል! በኩፍኝ ሳቢያ አካለ ጎደሎ ልጅ እንዳይወለድ ለመከላከል ሁሉም ሴቶች ከማርገዛቸው በፊት የኩፍኝ በሽታ ማለት measles, mumps እና rubella (MMR) ያካተተ የበሽታ መከላከያ ክትባት ለመውሰዳቸው ማረጋገጡ በጣም ጥሩ ዘዴ ነው።

ሴቶች የኩፍኝ/MMR በሽታ መከላከያን ከወሰዱ በኋላ ለአንድ ወር ያህል የሚሆን እርግዝናን ማስወገድና ነብሰጡር የሆኑትም እስከሚወልዱ ድረስ የበሽታ መከላከያ ክትባት መውሰድ የለባቸውም።

አንድ ሴት በቂ የኩፍኝን በሽታ መቋቋም ሃይል እንዳላት ለማረጋገጥ ከማርገዟ በፊት የደም ምርመራ ማካሄድ ጠቃሚ ነው። ምን እንኳን የበሽታ መከላከያ ቢወስድም፤ የደም ምርመራ ውጤቱ አለመኖሩን ወይም አነስተኛ የኩፍኝ በሽታ መቋቋሚያ ሃይል ካሳየ የኩፍኝ MMR ወይም rubella ክትባት መሰጠት አለበት። ከዚያም ክትባቱ በቂ የመከላከያ ሃይል ማበርከቱን ለማረጋገጥ ከስድስት ወይም ከስምንት ሳምንታት በኋላ የደም ምርመራ ማካሄድ።

በአውስትራሊያ ውስጥ ለህጻናት በሞላ ከአንድ አመት እድሜ ጀምሮ ሁለት የተለያዩ መጠን ያላቸው የMMR (የኩፍኝ፣ ጀሮ ደግፍና የጀርመን ኩፍኝ) በሃገርአቀፍ የበሽታ መከላከያ ፕሮግራም እንደመሆኑ መጠን ክትባት ይወስዱ ዘንድ ይደረጋል። በዚህ ክትባት ሶስቱንም በሽታዎች ይከላከላል።

ከ1965 ዓ.ም በኋላ የተወለዱ ታዳጊ ህጻናትና ጎልማሶች ለኩፍኝ በሽታ መቋቋሚያ ሃይል ሊያጥራቸው ይችላል። እነዚህ ሰዎች በቀላሉ ሊታመሙና በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ሁለት ጊዜ የMMR ክትባት ለመውሰዳቸው የሚያሳይ ሰነድ ካላቸው በስተቀር ወይም የደም ምርመራ ውጤት የMMR በሽታ መከላከያ ክትባት እንደሚያስፈልግ ካሳየ ይሆናል። ወንዶች፣ ሴቶችና ህጻናት የMMR በሽታ መከላከያ ክትባት መውሰዱ እነዚህ በሽታዎች በህብረተሰቡ እንዳይስፋፉ ለመከላከል ነው።

## ማን ነው በይበልጥ ለአደጋ የሚጋለጠው?

በልጅነት ወቅት የኩፍኝ ክትባት ፕሮግራም በማይሰጥበት የዓለም ዙሪያ ያሉ አገሮች። ሰዎች ከነዚህ አገር ወደ አውስትራሊያ የተሰደዱ፣ ይህም በነዚህ አገሮች የበሽታ መከላከያ ላይኖር ሲችል በተለይ ከ4 ዓመት እድሜ በኋላ ለመጡ ሰዎች ይሆናል። በተለይ ከኤሲያና አፍሪካ አገር ለተወለዱ ሴቶች ቀደም ሲል መከላከያውን ስላልወሰዱ ከማርገዛቸው በፊት የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባትን መውሰድ አለባቸው።

**በልጅነት ጊዜ በኩፍኝ በሽታ ቢያዙም ስለዚህ ለቀጣይ ሕይወት ዘመን ኩፍኝ አይዝም ለማለት አያስተማምንም። የሰውነት የበሽታ መቋቋሚያ አቅም መኖሩን ለማረጋገጥ ከእርግዝና በፊት በደም ምርመራ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።**

## የበሽታ መከላከያ ክትባት የት ነው የሚሰጠው?

በአካባቢዎ ባለ ሀኪም፣ በወሊድ መቆጣጠሪያ ክሊኒክ፣ በማህበረሰብ ጤና ጥበቃ ክሊኒክና በአካባቢ የበሽታ መከላከያ አገልግሎት በኩል የኩፍኝ/MMR ክትባት ማቅረብ ይችላሉ።

## የሚፈጠር ችግር REACTIONS

በእርግዝና ወቅት በኩፍኝ/ጀሮደግፍ/ጀርመን ኩፍኝ/MMR ክትባት የሚከሰተው ችግር ከኩፍኝ በሽታ ችግር ጋር ሲወዳደር በጣም አነስተኛ ነው። ከተለመዱት ችግሮች ውስጥ የበሽታ መከላከያ ከወሰዱ በኋላ ከአምስት እስከ አስራ ሁለት ቀናት የሚሆን ድህና አለመሆን፣ ትኩሳት፣ የእጢዎች ደም ስር መገታተርና በቆዳ ላይ ሽፍታ መታየት ናቸው። የበሽታ መከላከያ የወሰዱ ሰዎች በሽታውን ለሌላ ሰው አያስተላልፉም። በክትባቱ ምክንያት የሚከሰት ከባድ ችግር በጣም አነስተኛ ሲሆን ምናልባት ክትባቱን ከወሰዱት ከሚሊዮን ሰዎች አንድ ወይም በታች ቢሆን ነው። ስለሚያስከትለው ጥቅምና ጉዳት ከሀኪምዎ ጋር መወያየት ይቻላል።